# ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ ዉጪ አገር ወጥተው የሚመለሱበትን የጉምሩክ ስነስርዓት አፈፃፀም ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 171/2013

ገቢዎች ሚኒስቴር

ግንቦት 2011 ዓ.ም

## ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ ዉጪ አገር ወጥተው የሚመለሱበትን የጉምሩክ ስነስርዓት አፈፃፀም ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 171/2013

ዕቃዎች በጊዜያዊነት ከአገር ወጥተው የሚመለሱበትን ሁኔታ በመመሪያ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

ዕቃዎች በጊዜያዊነት ከአገር ወጥተው በሚመለሱበት ጊዜ ስለሚኖረው የቀረጥና ታክስ አከፋፈል ሁኔታን በመመሪያ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ የገቢዎች ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 180 ንዑስ ቁጥር (2) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ ወጪ አገር ወጥተው የሚመለሱበትን የጉምሩክ ስነስርዓት አፈፃፀም ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 171/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፦

1) "ዕቃ" ማለት ማንኛዉም በጊዜያዊነት ወደ ውጭ አገር ወጥቶ የሚመለስ ዕቃ ነው፤
2) "ቱሪስት" ማለት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ለጉብኝት ከኢትዮጵያ ወጥቶ የሚመለስ የኢትዮጵያ ነዋሪ ነው፡፡
3) "የቱሪስት መገልገያ ዕቃ" ማለት ለቱሪስት መገልገያነት በጊዜያዊነት ከአገር ወጥቶ በተወሰነ ጊዜ ገደብ ውስጥ ተመልሶ ወደ አገር የሚገባ ዕቃ ሲሆን ተሽከርካሪን ይጨምራል፤
4) "ሚኒስትር" ወይም "ሚኒስቴር" ማለት የገቢዎች ሚኒስትር ወይም ሚኒስቴር ነው፤
5) "አዋጅ" ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለው) ነው፤
6) "ኮሚሽን" ማለት የጉምሩክ ኮሚሽን ነው፤
7) ሌሎች ቃላቶችና ሐረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በጊዜያዊነት ወደ ወጪ አገር በሚወጡ እና ተመልሰው በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. <u>በጊዜያዊነት ከአገር ስለሚወጡ እና ተመልሰው ስለሚገቡ ዕቃዎች</u>

1/ የሚከተሉት ዕቃዎች በጊዜያዊነት ከአገር ሊወጡ እና ተመልሰዉ አገር ዉስጥ ሊገቡ ይችላሉ

ሀ) ወደ ውጭ አገር ለሥራ የሚሄድ ሰው የሚሄድበትን ሥራ ለማከናወን የሚጠቀምባቸው ተሽከርካሪዎች፣ መሣሪያዎችና ማሽነሪዎች፤

ለ) ንግድን ለማስተዋወቅና ለባህል ልውውጥ፣ ወይም ለማናቸውም ዓይነት ትርዒቶች ወይም ኤግዚቢሽኖች የሚወጡ ዕቃዎች

ሐ) የምርት ሂደታቸውን በውጭ አገር አጠናቀው የሚመለሱ ዕቃዎች፤

መ) በአገር ውስጥ ሊጠገኑ የማይችሉ ተጠግነዉ የሚመለሱ ዕቃዎች፤

ሠ) የቱሪስት መገልገያ ዕቃዎች፤

ረ) ከኢትዮጵያ ውጭ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያላቸው የአገር ውስጥ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ለሥራቸው የሚያስፈልጓቸው ተሽከርካሪዎች እና መሳሪያዎች፤

ሰ) በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚጠበቅ ኃላፊነት ጋር በተያያዘ ለሰላም ማስከበር ወይም ለሌላ ተልዕኮ የሚውሉ ዕቃዎች፤

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በጊዜያዊነት ከአገር የወጡ ዕቃዎች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተመልሰው ወደ አገር ውስጥ መግባት አለባቸው፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ቢኖርም ለፕሮጀክት ስምምነት እና ለዓለም አቀፍ ተልዕኮ በጊዜያዊነት ከአገር የሚወጡ ዕቃዎች ከአገር የወጡበት ዓላማ እንደተጠናቀቀ ተመልሰው ወደ አገር ውስጥ መግባት አለባቸው፤

4/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ (4) መሰረት በጊዜያዊነት ከአገር የወጡ ዕቃዎች ተመልሰው ወደ አገር ውስጥ መግባታቸውን ለማረጋገጥ ከአገር ውስጥ ከሚወጣው ዕቃ ዋጋ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የጥሬ ገንዘብ ተቀማጭ ወይም አስገዳጅ የባንክ ጋራንቲ ወይም የኢንሹራንስ ቦንድ የዕቃዉ ባለቤት ለኮሚሽኑ መቅረብ አለበት፤

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው ቢኖርም እንደሁኔታው በጊዜያዊነት የሚወጡ ዕቃዎች ዋስትና ሳይቀርብባቸው እንዲስተናገዱ ኮሚሽኑ አሰራር ዘርግቶ ሊወስንና ሊፈጽም ይችላል፤

6/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) እና (3) ድንጋጌ ቢኖርም በቂ ምክንያት ሲኖር ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወጥተው የሚመለሱበትን የጊዜ ገደብ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ኮሚሽኑ የሚዘረጋዉን የአሰራር ስርዓት መሰረት በማድረግ ከአራት ወራት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል። የማራዘሚያ ጊዜዉ የተጠየቀዉ ከአራት ወራት በላይ የሆነ እንደሆነ በአሳማኝ ምክንያት የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ወይም ኮሚሽነሩ የሚወክለዉ የሥራ ኃላፊ ከአምስት ወራት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል።

5. <u>በጊዜያዊነት ከአገር የወጣ ዕቃ ተመልሶ ወደ አገር ውስጥ ባልገባ ጊዜ ስለሚፈፀም ሥነ-ሥርዓት</u>

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 መሰረት በጊዜያዊነት ከአገር የወጣ ዕቃ በጊዜ ገደቡ ተመልሶ ወደ አገር ውስጥ ያልገባ እንደሆነ የተያዘው ዋስትና ለመንግስት ገቢ ይደረጋል፤

2/ በጊዜያዊነት ከአገር የወጡ ዕቃዎች ወደ አገር ውስጥ የማይመለሱ መሆኑን በመግለጽ ሳኪው ጥያቄ ሲያቀርብ ዕቃዎቹ በጊዜያዊነት የወጡበትን የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት በመቀየር ዕቃን በቀጥታ ወደ ውጭ የመላክ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እንዲፈፀምባቸው ማድረግ ይቻላል።

6. <u>በማካካሻ ምርት ላይ የቀረጥና ታክስ ክፍያ አፈጻጸም</u>

1/ በጊዜያዊነት ለጥገና ወጥተው ተመልሰው ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ለጥገና በወጣው ወጪ ላይ ቀረጥና ታክስ ይከፈልበታል፤

2/ በጊዚያዊነት ከአገር የወጡ ዕቃዎች በመመሪያው አንቀፅ 3 የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኃላ ወደ አገር እንዲገቡ ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ የተያዘው ዋስትና ለመንግስት ገቢ ተደርጎ የዋስትናው 50 በመቶ መቀጫ ተከፍሎ ዕቃዎቹ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ይፈቀዳል።

7. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ መመሪያ ከመጽናቱ በፊት ተጀምረው ውሳኔ ያላገኙ ጉዳዮች በነበረው ሕግ መሠረት ውሳኔ ያገኛሉ።

8. <u>የተሻሩ መመሪያዎችና ሰርኩላሮች</u>

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ በዚህ መመሪያ በተሸፈነ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

9. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ _______ቀን 2011 ዓ.ም

አዳነች አቤቤ
የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር